ግሎባል ባንክ
ኢትዮጵያ
ለጋራ ስኬታችን

# ብርቱ አጋር



ቅፅ 1
ዕትም 1
ሐምሌ 2016 ዓ.ም

www.globalbankethiopia.com

ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ

ለጋራ ስኬታችን

# ማውጫ

02 የዋና ሥራ አስፈፃሚ መልዕክት
05 ርዕሰ አንቀፅ
10 የባንኩ ርዕይ ፤ ተልዕኮ ፤ እሴት
12 የባንኩ ስያሜና የንግድ ምልክት ለውጥ
16 የባንካችን ሙዚቃዊ ብራንድ ( ጄንግል )
20 የቅርንጫፍ ማስፋፊያ
22 ዲጂታል ባንኪንግ
24 ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት
26 ማህበራዊ ኃላፊነት
28 የዕድገትና የለውጥ ጉዞ አዲስ ምዕራፍ

**በማርኬቲንግና ኮሚዩኒኬሽንስ መምሪያ የተዘጋጀ**

**ማኔጂንግ ኤዲተር**፡- ቢኒያም ፍቃዱ
**ኤዲተር**፡- ተመስገን ፍቃዱ
**ዋና አዘጋጅ**፡- ዘመላክ ብርሀኑ
**አዘጋጅ**፡- ሀብቴ ጎዴ

**አድራሻ**

**ስልክ**፡፡- +251 115 58 12 45 **ኢሜል፡** marketinggbe@globalbankethiopia.com
**ዘምብራ፡** marketingandcommunicationsdepartment@debubglobalbank.local



**ተስፋዬ ቦሩ (ዶ/ር)**
ዋና ሥራ አስፈፃሚ

# የዋና ሥራ አስፈፃሚ መልዕክት


ይህንን መልእክት ሳጋራ ለግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ አ.ማ ቁርጠኛ ፣ ዲሲፕሊንድ እና ብርቱ ሰራተኞች ያለኝን ልባዊ አክብሮትና አድናቆት በማስቀደም በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ለተመዘገበው የላቀ ስኬት እንኳን ደስ አላችሁ ስል በታላቅ ክብር ነው።
ያሳለፍነው በጀት ዓመት በጉዟችን በፋይናንስ እና ፋይናንስ ነክ ባልሆኑ የአፈፃፀም መለኪያዎች እጅግ ከፍተኛ ስኬት የተጎናፀፍንበት ፤ አንገታችንን ቀና አድርገን እንድንጓዝ ያደረገ አፈፃፀም ባስመዘገብንበት ወቅት በመሆኑ በብዙ ፈተናዎች መካከል ውጤታማ መሆናችን ጽናታችንን እና አይበገሬነታችንን ከማሳየቱም በላይ እናንተ የባንካችን አመራሮች እና ሰራተኞች በተሰማራችሁበት የስራ ዘርፍ ብቁ እና እምነት የሚጣልባችሁ መሆናችሁን ያስመሰከራችሁበት ነው።

ውድ ሠራተኞች ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከአንድ ቢልየን ሃያ አምስት ሚሊዮን ብር በላይ ያልተጣራ ትርፍ ያስመዘገበ ሲሆን፤ የባንካችን ጠቅላላ የኀብት መጠንም ወደ 21 ቢሊዮን ብር ማሳደግ ችለናል። የባንኩን ካፒታል ወደ 5 ቢሊዮን ብር ለማድረስ ተግተን በሰራነው ስራ ያስመዘገብነው ወጤት አመርቂ ቢሆንም ቀጣዮቹ ዓመታት በብሔራዊ ባንክ የተቀመጠልንን የካፒታል እድገት ግብ ለማሳካት ጠንክረን የምንሰራበት ዓመት ነው ።

በተቀማጭ ገንዘብ አሰባሰብ እና የሰበሰበውን ኀብት መልሶ በማበደር የሃገርን ኢኮኖሚ እድገት በመደገፍ ረገድም ያሳለፍነው በጀት ዓመት ከፍተኛ ሚና የተጫወትንበትም ነው። በቴክኖሎጂ ዘርፍም የባንካችንን የኮር ባንኪንግ አገልግሎት ወደ ላቀ ደረጃ ከማሻገራችንም በላይ ዘመኑን የሚመጥን የዳታ ሴንተር በመገንባትም የባንኩን አገልግሎት በተሳለጠ መልኩ እንዲከወን የማድረግ ሥራችንን ያጠናከርንበት ወደፊትም በልዩ ትኩረት የምንሰራበት ጊዜ ነው።

በአንድ ቅርንጫፍና በጥቂት ሰራተኞች ስራውን የጀመረው ባንካችን በአሁኑ ወቅት የሰራተኞቹን ቁጥር ከ3000 በላይ ያሳደገ ሲሆን የቅርንጫፍ ብዛቱንም በመላው ኢትዮጵያ በማስፋት በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከ 225 በላይ አድርሷል። የደንበኞቻችንን ቁጥርም ከ1.5 ሚልየን በላይ በማሳደግ የበጀት ዓመቱን በተሳካ ሁኔታ ያጠናቀቅን ሲሆን ባንካችን በዘርፈ ብዙ መለኪያዎች በፈጣን የእድገትና የስኬት ጉዞ ላይ የሚገኝ ባንክ መሆኑን ለማወቅ አያዳግትም ።

ለደንበኞቹ ምቹ አገልግሎትን በመስጠት የደንበኞቹን እርካታ በመጨመር የባንኩን የዕድገት ጉዞ በቀጣዩ በጀት ዓመትም ከዚህ የተሻለ ውጤት የምናስመዘግብበት እንዲሆን ምኞቴ ነው። ይህንን ስኬት ሙሉ በሙሉ ባንኩን ወደ አዲስ የዕድገት ጉዞ እየወሰደው ያለ የህይወት ምዕራፍ በመሆኑ ባንካችሁን ለማሳደግ ሌት ተቀን ለምትለፉ ለናንተ ለታማኝ እና ትጉሃን ሰራተኞች አደራ እሰጣለሁ።



ይህን ስል ግን ወደፊት ያለው መንገድ ቀላል እንዳልሆነ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፡ በሚቀጥሉት ዓመታት ውስጥ በርካታ ነገሮች ሊለወጡ እንደሚችሉ እምኑ ነው። የአዳዲስ እና የውጪ ባንኮች ወደሃገራችን መግባት፤ የደንበኞች ፍላጎት ከግዜ ወደግዜ እያደገ እና እየተለወጠ መምጣት፣ አጠቃላይ የሃገራችን የማክሮ ኢኮኖሚ መዋቅር ላይ ሊፈጠር የሚችል ለውጥ ፣ የቴክኖሎጂ እድገቱ እና ሌሎችም ጉዳዮች ወድድሩን ከባድ ሊያደርጉብን እንደሚችሉ ይገመታል። በመሆኑም በዚህ ውስጥ ጠንክሮ መውጣት ለባንኮች አማራጭ የሌለው ጉዳይ በመሆኑ ትጋታችሁ ከምንግዜውም በላይ ሊሆን እንደሚገባ አደራ እላለው።

እያንዳንዱ ሰራተኛ ባንኩን እና ስራውን ከመውደድ እንዲጀምር፣ ፍላጎቱን ለማሳካት የሚቻለውን ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት፣ እራሱን እንደ ባንክ ባለሙያ በመሳል እና ከገደቡ በላይ በመስራት ባንካችን እንዲያድግ በእራሳችሁ ላይ ኢንቨስት እንታደርጉ እጠብቃለሁ። በፕሮፌሽናሊዝም ረገድ ያላችሁ የእድገት ደረጃ የዚህን ባንክ የወደፊት እድገት እንደሚወስን እናምናለን። የባንካችን ማናጅመንት እጅግ ጠቃሚ የሆነውን የሰውን ሀብትን ለማልማት፣ ለማሰልጠን፣ ዕውቅና ለመስጠት እና ወደ ላቀ ከፍታ ለማሻገር በትጋት እንደሚሰራ ለማረጋገጥ እወዳለሁ።



የባንኩ የማኔጅመንት አባላት

ግሎባል ባንክ
ኢትዮጵያ
ለጋራ ስኬታች

# ገንዘብ
# በሚያስፈልግዎ
# ጊዜ ሁሉ!



# ርዕሰ አንቀጽ

በተቋም/መስሪያ ቤት ውስጥ ያሉ የግለሰቦችን ስብስብ ወደ አንድ አቅጣጫ/ግብ ለማፋሰስ ደግሞ ተቋማዊ የስራ እና የአሰራር ባህልን በመፍጠር ሁሉም እንዲተዳደርበትና እንዲመራበት ማድረግ ተቋሙ የሚመራበት ፓሊስዎች፣ የአሰራር ሁኔታዎች፣ ደንብና መመሪያዎች ከዚህ ባህል ቢቀዱ መልካም እንደሆነ ብዘዎችን ያግባባል።

ስለ ተቋም ሲወራ የመጀመሪያው ጉዳይ በተቋሙ ውስጥ የሚገኙ ሰራተኞች ናቸው። እነዚህ ሰዎች ወይም ሠራተኞች ደግሞ የየራሳቸው እሳቤ፣ የአኗኗር ዘይቤ፣ ለነገሮች ያላቸው ምልከታ፣ የተሰሩበት የስነ-ልቦና ወቅር፣ የአስተሳሰብና አመለካከት ሚዛናዊነትና ሌሎችም ጉዳዮች በሰዎች መካከል ልዩነቶች እንዲፈጠሩ ያደርጋል። በመሆኑም ሰዎች በተቋም ሲሰበሰቡ ልዩነቶችን ወደ ጎን ትተው ለተቋማዊ ለውጥና ስኬት በጋራ የመስራት ተገቢነት ላይ በርካታ የማህበራዊ ሳይንስ እና የስነ-ልቦና ምሁራን ልዩነት የላቸውም ።



የሚገነባ የስራ ባህል ደግሞ ሁሉም ሠራተኞች ባላቸው የስራ ግንኙነት ሁሉ ተግባብተው የሚሰሩበትና ለጋራ ዓላማ በጋራ የሚተጉበት፣ ሁሉም የተግባቦት ሥርአቶች የተቋሙን ባህል ያማከሉና የተሰናሰለ እንዲሆኑ በማድረግ ለጋራ ስኬት በጋራ የሚሰራበት መንገድ መፍጠር ተገቢም አስፈላጊም ከመሆኑ ባሻገር በውድድር ሜዳው ለአሸናፊነት የሚያበቃ ቁልፍ መሳሪያ መሆኑን ልብ ሊባል ይገባል። በተቋም ውስጥ የሚፈጠር የስራ ባህል ከተቋም ውጭ ያሉትንም ባለድርሻ አካላት ታሳቢ ያደረገ ዘመኑን የዋጀ በቻል የቀደመ ሲሆን በውድድር ሜዳው ላይ አሸናፊነትን የሚያጎናጽፍ መተኪያ የሌለው መሳሪያ ነው።

ተቋማዊ ባህል መፍጠር የአስተሳሰብና የድርጊት ለውጥ የማምጣት ሁነኛ ሥራ በመሆኑ ዘመናዊነትን የተላበሰና በቴክኖሎጂ የሚታገዝ እንዲሆን ማስቻል ለድርድር የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም።
ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ እራሱን መልሶ በመለወጥና በመገንባት ሂደት ውስጥ ልዩ ትኩረት ከሰጣቸው ሥራዎቹ መካከል ዋነኛው በባንኩ ውስጥ የባህል አብዮት በመፍጠር የባንኩ ቤተሰቦች አዲስ ባህል እንዲላበሱ ማስቻል ቀዳሚ ተግባር ተደርጎ ተሰርቶበታል ፤ ውጤትም ተገኝቶበታል።


ድርጅታዊ/ተቋማዊ ባህል የድርጅቱ ሰራተኞች/እንደራሴዎች፣ ባለድርሻ አካላት፣ ያገባኛል ባዮችና ሌሎችም ከባንኩ ጋር ያላቸው መስተጋብርን የሚወስን ስታንዳርድ/ልኬትን የሚያስቀምጥ ማንኛውም ግንኙነት በዚህ ስታንዳርድ/ልኬት መሠረት የሚቃኝና የሚመራ መአዘው የጋራ ስኬትን የሚያውድ መሆኑን ማረጋገጥ የአመራሩ ዋነኛ ሚና ነው።
በመሆኑም ባንኩን አዲስ ተቋማዊ ባህልን ለማስተዋወቅ ከሪብራንዲንግ ሥራው ጋር በተያያዘ በርካታ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን ውጤታቸው ከግዜ ወደ ግዜ አመርቂ እየሆነ መጥቷል። ይህ ውጤት ቀጣይነት እንዲኖረው ደግሞ ሁሉን አቀፍ ተቋማዊ የባህል ምሰሶዎችን/ማዕዘናት በማቆም ሁሉንም በአንድ ጥላ ስር የሚያሰባስብ ለታላቁ መዳረሻ ደግሞ ብርቱ አጋር የሚሆን ተቋም ለመፍጠር እየተሰራ ነው ። ጉዞውም መልካም ነው።

ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ
ለጋራ ስኬታችን

# ወርቃማ ወለድ በወርቃማው ቁጠባ!!

# 9% ወለድ

በወርቃማ የቁጠባ ሒሳብ አገልግሎት የ9% ወለድ ተጠቃሚ ይሁኑ ።



# ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ የተገነባባቸው
# ተቋማዊ የባህል ማዕዘናት

## ሠዓት አክበባሪነት

ሠዓት አክበባሪነት (Punctuality) የምንለው ቃል ጥሬ ትርጉሙ ሠዓት አክባሪነት ቢሆንም በርካታ ኀላፊነትን በውስጡ የሚይዝ ነው። ይህኛው ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ የስራ ባህል የተሰራባት የመዓዘን ድንጋይ ሠዓት አክባሪነት ስንል በጊዜው መገኘት ወይም የቀጠሮን ሰዓት ማክበር ብቻ ሳይሆን የተቀመጠ ስታንዳርድ/ልኬቶች ወይም መመዘኛዎች ማክበርንም በውስጡ ያቀፈ ነው።

ሠዓት አክባሪነት የግሎባል ባንክ ቤተሰቦች ለጊዜ፣ ለመመዘኛዎች አሊያም ለስታንዳርዶች ያላቸው ግንዛቤ ፣ አመለካከት አልያም የተግባር ወሃ ልክ ነው። በግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ የአሰራር ሥርዓት ውስጥ ሁሉም ስራ/ተግባር ከተቀመጠለት የግዜ ገደብ በፊት ይሰራል። ከተቀመጠለት የጥራት መመዘኛ በላይ ይፈፀማል የሚል የባህል አበዮት ነው።

ይህ የባንኩ ለውጥ ከተቋማዊ አሰራር ባሻገር በእያንዳንዱ የባንባችን ሰራተኞች የኑሮ ውህደት/ሂደት ውስጥ አለማርፈድን ይሰብካል ነው። ለመማር ያለማርፈድ፤ ለመለወጥ ያለማርፈድ፣ ለትዳር ያለማርፈድ፣ ለአዲስ አስተሳሰብና ለውጥ ያለማርፈድ፣ ራስን ለመቀየር በሚደረግ የህይወት ሩጫ ውስጥ ያለማርፈድ እና ሌሎችም እንደሆን ልብ ሊባል ይገባዋል።

ሰዓት አክባሪነት አልያም የተቀመጡ ስታንዳርዶችን አክብሮ ማስከበር ደግሞ የአክብሮት፣ የመያተኝነት፣ የታማኝነት መገለጫዎች በመሆናቸው ነው።

እነዚህ በተገቢው መልኩ ተሟልተው ሲገኙ የደንበኞች እርካታ ይጨምራል ፤ የደንበኞች እርካታ በመኖሩ ምክንያት ደግሞ የዓብሮት ድግግሞሽ /የገበያ ልውውጥ ድግግሞሽ/ ይኖራል።

ይህ ድግግሞሽ የባንኩን ገቢ ያሳድጋል፣ የባንኩ ገቢ ሲያድግ ምርትና ምርታማነት ይጨምራል። የምርታማነት መጨመር ደግሞ ሁሉም በደረጃው በሰራው ስራ እና ባገኘው ውጤት ደስተኛ እንዲሆን ያስችለዋል። ደስተኝነቱ የሚናበብና የተዋሃደ የስራ ቡድን/Team/ እንዲኖር ያደርጋል።

እንዲህ አይነቱ የስራ ቡድን ውስጥ ደግሞ ምክንያታዊ የሥራ ሂደት ሚዛናዊነት እንዲጎለበት ያስችለዋል።

## የቢሮ ንፅህና እና ስታንዳርድ ማስጠበቅ

የባንካችን የብራንድ እሳቤ ካስተዋወቃቸው የባህል ማዕዘኖች ውስጥ ሌላኛው የቢሮ ንፅህና እና ስታንዳርድ የማስጠበቅ ሥራዎች ናቸው። ብራንዱ በሁሉም ቦታ ወጥነቱን ጠብቆ እንዲቀጥል ከሚሰሩ ስራዎች ውስጥ የአገልግሎት መስጫ ቦታዎችን ለሰራተኞች፣ ለደንበኞችና ሌሎች ባለድርሻዎች ምቹ የማድረግ ሥራ ሌላኛው ገፅታ ነው።

በዚህም የባንኩ ቅርንጫፎች ሶስት ደረጃ ያላቸው ሲሆን ፕሪምየም የሚባለት አሁን በዋናው መስሪያ ቤት ህንፃ የሚገኙት ስታዲየምና ኑር ከወለድ ነፃ ቅርንጫፎች፣ የወርቅ ደረጃ ተብለው የተለዩና ስታንዳርድ/መደበኛ የሚባለት ደግሞ በተለይም ከአዲሱ ብራንድ ትግበራ በኋላ እየተከፈቱ ያሉ ቅርንጫፎችንም ያካትታል።

## የአለባበስ ስነ-ስርአት

እንደ ባንክ ባሉ ተቋማት ውስጥ የሰራተኞች የአለባበስ ሥርአት ስለባንኩ የሚናገረው ነገር ብዙ ነው። በመሆኑም ሁሉም የባንኩ ሠራተኞች በወጣው የአለባበስ ሥነ-ስርአትና ደረጃ መሰረት በመቅረብ ሠራተኞቹ ሁሉ ሙያተኞች መሆናቸውንና ለተግባቦት ምቹ መሆናቸውን በማረጋገጥ የአመለካከታችንንና የሥራዎቻችንን ንፅህና ለሌላኛው ወገን ሊያሳይ በሚችል መልኩ ተቃኝቶ የራሱ መመሪያ ወጥቶለት በመተግበር ላይ ይገኛል።

ይህም ተግባር ሁሉም የባንኩ ስራተኞች ሙያተኞች/ ኘሮፌሽናልስ/ መሆናቸውን ከማሳየቱም በላይ የባንኩን ብራንድ ወጥነት የሚያሳይ፣ የሰራተኞች ትኩረትና ምርታማነት የሚያሳድግ፣ ፍትሃዊነትና አካታችነትን የሚያረጋግጥ፣ ምርታማነትና ደህንነትን የሚሰብክ ጥቅል አላማን ያነገበ በመሆኑ እንደ ተማሪ ዩኒፎርም የማልበስ እሳቤ እንዳልሆነ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል።

## ወጪ ቆጣቢነት

ሌላኛው የግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ ተቋማዊ ባህል ወጪ ቆጣቢነት ነው። ወጪ ቆጣቢነት ሲባል በግርድፍ አስተሳሰቡ ወጪ ያለማውጣት ሳይሆን ምክንያታዊ የወጪ አስተዳደር ሥርአትን በመዘርጋት ወጪ ገቢ ተኮር እንዲሆን ማስቻል ነው። ይህም ተወዳዳሪነትን አጎልብቶ ትርፋማነትን ያሳድጋል፣ የፋይናንስ መረጋጋትና እድገትን ያሳልጣል፣ ምክንያታዊ የአደጋ ስጋት /Risk/ አስተዳደር ስርአት በመዘርጋት ለመስራት ያስችላል።

በዚህም እያንዳንዱ ውሳኔ ዕውቀት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ያግዛል። ከምንም በላይ ትርፋማነትን አሳድጎ የባለአክሲዮኖችን ድርሻ ከፍ ያደርጋል። ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ በዚህ ተቋማዊ ባህል በመመራት ከፍተኛ የዕድገት ጉዞውን አጠናክሮ ይቀጥላል።

ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ
ለጋራ ስኬታች

# ጥሬ ገንዘብ መያዝን
# የሚያስቀር!

በግሎባል የዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎታችን
ያለ ጥሬ ገንዘብ ይገበያዩ።



## ርዕይ

እ.ኤ.አ  በ 2035 በአሰራር ልህቀት በምስራቅ አፍሪካ ቀዳሚ ባንክ መሆን

## ተልዕኮ

ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ አ.ማ በበሳል አመራር እና በሰለጠነ የሰው ሃይል በመታገዝ ፣ ለስራ የሚመጥንና ብቃት ያለው ሰራተኛን በመመልመልና በማሰልጠን  እንዲሁም ዘመኑን የዋጀ ቴክኖሎጂን በመጠቀም  ለደንበኞቹና ለባለድርሻ አካላት  የላቀ የባንክ አገልግሎት መስጠት

## ዕሴት

- የደንበኞቹ ብርቱ አጋር መሆን
- የሰለጠነ የሰው ሃይል  ማፍራት
- ብዝሃነትን እና የቡድን ስራን ማሳደግ
- ዘወትር  መማር
- ለሰራተኞቹ ምቹ የስራ አካባቢን መፍጠር
- በቅንነት መስራት
- ህብረተሰቡን ማገልገል

ግሎባል ባንክ
ኢትዮጵያ
ለጋራ ስኬታች

# ይደውሉ

ለፈለጉት መረጃ በ8118
ነፃ የስልክ መስመር ይደውሉ



# የባንኩ ስያሜና የንግድ ምልክት ለውጥ

ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ ከሚሰጠው የባንክ አገልግሎት አንፃር ዘመኑን የሚመጥን ካስቀመጠው እስትራቴጂክ እቅድ እንዲሁም ዓላማና ግብ አንጻር አብሮ የሚሔድ የስያሜና የንግድ ምልክት ለውጥ አድርጓል። ይህ ለውጥ ዝም ብሎ ለውጥ ሳሆን ስር ነቀል የአስተሳሰብና የአሰራር ለውጥን በማምጣት ከዘመኑ ጋር አብሮ እየዘመነ ጊዜው የሚጠይቀውን ዕውቀትና የአሰራር ዘዴዎችን በመከተል ለጋራ ስኬት የዘርፉን ከፍተኛ ባለሙያዎች ፤ ባለአክሲዮኖች ፤ ሰራተኞችና ደንበኞችን በማሳተፍ ከዚህ በፊት ሲጠቀምበት የነበረውን ስያሜና የንግድ ምልክት በተሳካ ሁኔታ ቀይሯል ፡፡

ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ
ለጋራ ስኬታችን

**ዛሬ ላይ ሁሉም ነገር ተሳክቶ ባንካችን « ኢትዮጵያ» የሚለውን ስም የያዘ የመጀመሪው የግል ባንክ መሆን ችሏል።**

> “ ኢትዮጵያዊ ሆኖ አለም አቀፍነት ዘመንን መቅደም ነው ግሎባል ባንክነት ”

በማለት የባንኩን ታላቅ ራዕይና ስኬት ያነሳል !!

ይህ ሁለንተናዊ ለውጥ ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ ራሱን በአዲስ ገጽታ ፤ በአዲስ ቀለምና የንግድ ምልክት ወደ ገበያው ገብቶ ተወዳዳሪ እንዲሆን ከማስቻሉም በላይ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለውና ከጊዜው ጋር በመዘመን በከፍተኛ የለውጥና የስራ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዳለም ማሳያ ነው ፡፡




# No more cash

If you have our Global ATM card, you don't have to come to our bank branch to withdraw money.

# የንግድ ምልክት(ሎጎ) ፍቺ

**የባንካችን የንግድ ምልክት (ሎጎ) ዋና ማጠንጠኛ የበር እና የቁልፍ ምልክት ሲሆኑ ትርጉማቸው እንደሚከተለው ይቀርባል**

**የባንካችን የንግድ ምልክት ላይ ያለው « የበር » ምልክት ሲተረጎም**

አዲስ እድል፤ አዲስ ምዕራፍ ፤ የላቀ መዳረሻ ፤ ለሁሉም ክፍት የሆነ ፣ ሁሉም ሰው በእኩልነት የሚስተናገድበት መግቢያ፤ ሁሉም ሰው ማሳካት ወደሚፈልገው ራዕይ የሚገባበት የጋራችን ስኬት ላይ የምንደርስበት የተስፋ በር/ከፍታ ነው ።

**የባንካችን የንግድ ምልክት ላይ ያለው « የቁልፍ » ምልክት ሲተረጎም ፡- ሚስጥር ጠባቂ መሆናችንን ያረጋግጣል**

ባንካችን ለደንበኞቹ የስኬታቸው ቁልፍ አጋር መሆኑን እንዲሁም ፤ ደህንነቱ የተጠበቀና አስተማማኝ የባንክ አገልግሎት ለመስጠት ማለማችንን ለማሳየት የተጠቀምነው ምልክት ነው ።

**የባንካችን የንግድ ምልክት ላይ ያለው « የ G እና B » ፊደላት ትርጉም**

በቀላሉ የማይበገር ማንነት ፣ አቃፊነት ፣ ወንድማማችነት ፣ ደስተኝነት እና ለመልካም ነገር ሁሉ በድፍረት ፋና ወጊ መሆናችንን የሚያሳይ ነው።

| B | G |
|---|---|
| Big Hearted | Brave |
| Considerate | Brilliant |
| Delighted | Brotherly |
| Festive | Brisk |

ይህ ስር ነቀል የሆነ ለውጥ ባንካችን ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የብራንድ ባለቤት እንዲሆን ከማድረጉም በተጨማሪ ራሳቸውን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ መንገድ ለጀመሩ ብርቱዎች ወደ ታላቁ መዳረሻቸው ለሚያደርጉት ጉዞ «ብርቱ አጋር» ሆነን በታማኝነት እና በአጋርነት ስሜት አብረናቸው በመዘለቅ ስኬታቸው ስኬታችን መሆኑን ማሳየት ዋነኛ መገለጫው ይሆናል።

ግሎባል ባንክ
ኢትዮጵያ
ለጋራ ስኬታችን

# ካርድዎን ከያዙ በቂ ነው



# የባንካችን ሙዚቃዊ ብራንድ ( ጂንግል )

የባንካችን አዲስ ስያሜና የንግድ ምልክት እንዲሁም ሁለንተናዊ የዕድገትና የለውጥ ጉዞ ከፍ ባለ መልኩ እንዲተዋወቅና እንዲደመጥ ለማስቻል ለማስተዋወቂያና ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል ሙዚቃዊ ብራንድ ( ጂንግል ) በሀገር አቀፍና በአለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ በሆነው የሙዚቃ አቀናባሪ ቴዎድሮስ መኮንን ወይም በመድረክ ስሙ « ቴዲ ማክ » ተዘጋጅቶ በይፋ የባንካችንን ከፍታ በማስተዋወቅ ላይ ይገኛል፡፡

> “ በአብሮነት የሚዘልቅ እስከ መጨረሻ
> ግሎባል ባንክ ነው ብርቱ መዳረሻ ”



ቴዎድሮስ መኮንን(ቴዲ ማክ)
የዜማው ደራሲ



ዘመላክ ብርሃኑ
የግጥሙ ደራሲ

# ዛሬውኑ ይክፈቱ!

ቀም ያለ የ9% ወለድ የሚያገኙበትን የግሎባል ባንክ ወርቃማ የአረጋውያን የቁጠባ ሒሳብ ዛሬውኑ ይክፈቱ።



ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ

# የግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ
# ሙዚቃዊ ብራንድ ( ጂንግል ) ግጥም

በላቀ አስተሳሰብ
ራሱን ቀይሮ
ዓለም አቀፍ ዕውቀት
ከሀገር አስተባብሮ ።
በደንበኞች ስኬት
ራሱን የሚለካ
በአገልግሎት ጥራት
ሁሉን የሚያረካ ።
ኢትዮጵያዊ ሆኖ
ዓለም አቀፍነት
ዘመኑን መቅደም ነው
ግሎባል ባንክነት ።
ይመርጡታል እንጂ
መች ይወዳደራል
ለጋሪችን ስኬት
ጠንክሮ ይሰራል ።
በአብሮነት የሚዘልቅ
እስከ  መጨረሻ
ግሎባል ባንክ ነው
ብርቱ መዳረሻ ።

ኑ ! አብረን እንደግ
ኑ ! አብረን እንስራ
ዘመኑን ከዋጀው
ከግሎባል ጋራ ።
ራሱን የፈጠረ  እንደ አዲስ ሞሽሮ
ቀርጠኛ የሆነ ለመለወጥ አብሮ
ግሎባል ባንክ ነው በዚህ የሰመረለት
ያቀደው በሙሉ ቀድሞ የተሳካለት ።
በህይወት ጉዞ ውስጥ በዕድገት ጎዳና
ወደ እርስዎ ራዕይ አብሮ እያቀና
ሙሉ ነው ባንካችን ለሁሉም ይበቃል
ግሎባል የሚል ስም ሁሉንም ያነቃል
እድገትና ስኬት በአንድ ላይ ፈሰሱ
ሁሉ በእጅዎ ላይ ነው የድርሻዎን ያንሱ ።
ኑ ! አብረን እንደግ
ኑ ! አብረን እንስራ
ዘመኑን ከዋጀው
ከግሎባል ጋራ ።

የግጥሙ ፀሀፊ  ፡-  ዘመላክ ብርሃኑ



ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ
ለጋራ ስኬታች
ክፍያዎን
ፈፅመዋል!
ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ
የግሎባል ዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎትን በመጠቀም ክፍያዎን ፈፅመዋል!

# የቅርንጫፍ ማስፋፊያ

ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ ለደንበኞቹ ያለውን ተደራሽነት በማስፋት በአዲስ አበባና በተለያዩ የክልል ከተሞች ከ225 በላይ ቅርንጫፎችን ከፍቶ አገልግሎት እየሰጠ ሲሆን በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ብቻ 73 ( ሰባ ሶስት ) ቅርንጫፎችን በመክፈት ለደንበኞቹ ብርቱ አጋር መሆኑን በተግባር ማሳየት ችሏል




የቅርንጫፍ ማስፋፋት ስራችን በየአከባቢው ያለንን ተደራሽነት ከማስፋትም በላይ የገበያ ድርሻችንን እንድናሳድግ ፤ የተለያዩ የኢኮኖሚ አወታሮችን ማገልገል እንድንችል ፣ የደንበኞቻችን ምቾት ከአገልግሎት ጥራት ፣ ከጊዜ እና ከላስፈላጊ ገንዘብ ብክነት ይታደጋል ብለን በፅኑ እናምናለን። ይህም በእኛና በደንበኞቻችን መካከል ያለውን መልካም የስራ ትስስር በማዳበር ለጋራ ስኬታችን በጋራ አብረን እንድንሰራ ያሰችለናል።

የቅርንጫፍ ከፈታ ስራዎቻችን የብራንዳችንን ተደራሽነት በማስፋት የተሳለጠ አገልግሎት ከመስጠትም በላይ አዳዲስ የባንክ ተጠቃሚዎችን ወደ ባንካችን በመሳብ ረገድም የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ነው።


ግሎባል ባንክ
ኢትዮጵያ
ለጋራ ስኬታች
የልጆች
የቁጠባ ሂሳብ!
አሁኑኑ ወደ ባንካችን ብቅ ብለው ለልጆችዎ
የወደፊት ህይወት ብሩህ ተስፋ የሆነውን
የልጆች የቁጠባ ሂሳብ ይክፈቱ
Children

# ዲጂታል ባንኪንግ

ባንካችን በመደበኛ ቅርንጫፎች በኩል ያለውን ተደራሽነት በማስፋት ለደንበኞቹ ምቹና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት በባንክ ቴክኖሎጂው ዘርፍ የሰራቸው ስራዎች ፍሬ ማፍራት የጀመሩ ሲሆን ቅርንጫፎቹን በኮር ባንኪንግ ቴክኖሎጂ በማስተሳሰር፣ የዲጂታል ባንኪንግ ( የሞባይል ባንኪንግ ፣ የካርድ ባንኪንግ ፣ የኢንተርኔት ባንኪንግ) አገልግሎቶችን ለደንበኞቹ እየሰጠ ከመሆኑም ባሻገር ያለምንም ክፍያ አገልግሎት የሚያገኙበት የጥሪ ማዕከል 8118 ሥራ በማስጀመር የደንበኞቹን ፍላጎት ለማሟላት ተግቶ እየሰራ ይገኛል ። ዘመናዊ የአንድ ማዕከል የዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎት መስጫ ማዕከልም አስገንብቶ ወደ ሥራ ገብቷል፡

በተጨማሪም ባንካችን ከአጋር ድርጅቶች ፣ ኢትዮ ቴሌኮም ፤ ሳፋሪ ኮም፤ ደራሽ፣ ጉዞጎ፣ ካቻ፣ ኢትስዊችና ሌሎችም ጋር በጥምረት እየሰራ ይገኛል። ይህ የዲጂታል ባንኪንግ ሲስተም ከምንሰጠው ዓለም አቀፍና ሀገር በቀል የባንክ አገልግሎት አንፃር የባንካችንን የዕድገት ጉዞ የሚመጥን እንዲሁም ካስቀመጥነው እስትራቴጂክ እቅድ ጋር አብሮ የሚሔድና በገበያው ውስጥ ያለንን ተወዳዳሪነት ይበልጥ ለማጠናከር የሚያግዝ ነው።



ethio telecom | Safaricom | Guzo GO | Kacha | ETHSWITCH | ደራሽ

ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ
ለጋራ ስኬታች

# ለምቾቶ ቅድሚያ እንሰጣለን

ፈጣን እና አስተማማኝ የሆነውን የግሎባል ዲጂታል ባንኪንግ
አገልግሎት በመጠቀም ዲጂታል አለምን ይቀላቀሉ።



# ከወለድ ነፃ
# የባንክ አገልግሎት

ከወለድ-ነፃ የባንክ አገልግሎት የሸሪዓ የፋይናንስ መርሆችን በመከተል በአገልግሎት ወቅት ምንም አይነት ወለድ መክፈልም ሆነ መቀበል ላይ ያልተመሰረተ እንዲሁም በሸሪዓ በተፈቀዱ ስራዎች ላይ ብቻ የሚሳተፍ የራሱ የሆነ አሰራር ያለው ሆኖ ማንኛውም አገልግሎቱን መጠቀም ለሚፈልግ ደንበኛ የቀረበ አማራጭ የባንክ አገልግሎት ነው።

ባንካችን የሸሪዓ የፋይናንስ መርሆችን በመከተል ሙሉ ለሙሉ ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት የሚሰጡ አራት ቅርንጫፎችን ጨምሮ በሁሉም የባንካችን  ቅርንጫፎች ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።



ግሎባል ባንክ
ኢትዮጵያ
ለጋራ ስኬታችን

# የሸሪዓ የፋይናንስ መርሆችን የተከተለ!

የሸሪአ ህግጋትን በጠበቀ መልኩ የተቀማጭ ሂሳብ፣ የፋይናንስ እና
የመሳሰሉት አገልግሎቶችን እንሰጣለን፡፡

# ማህበራዊ
# ኀላፊነት

ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ በተለያዩ አገራዊና ማህበረሰባዊ ጉዳዮች ላይ በመሳተፍ ማህበራዊ ኀላፊነቱን በመወጣት ለአገርና ለወገን ብርቱ አጋር መሆኑን በተግባር ያሳየ የፋይናንስ ተቋም ነው ። በዚህም በርካታ ባለድርሻዎችን በማሳተፍ ለሀገር ሁለንተናዊ እድገት ከፍተኛ ሚና እያበረከተ የሚገኝ ሲሆን አስታዋሽ ያጡ ወገኖችንም በአይነት እና በገንዘብ በመደገፍ የክፉ ቀን ደራሽ መሆኑን አስመስክሯል።:



**ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ለበዓል መዋያ ሲያበረክት**



**ሠራተኞች**
ደም በመለገስ ላይ

ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ
ለጋራ ስኬታችን

# ለስኬትዎ ብርቱ አጋር



# የዕድገትና የለውጥ
# ጉዞ  አዲስ ምዕራፍ





### የባንካችን የወደፊት ዋና መስሪያ ቤት የሚገነባበት ቦታ

ባንካችን የጀመረውን የዕድገትና የስኬት ጉዞ በማስቀጠል በመሀል አዲስ አበባ በተለምዶ የፋይናንስ ተቋማት መናህሪያ በሚባለው ሜክሲኮ አካባቢ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለዋና መ/ቤት ህንፃ ግንባታ  5,500 ካሬ ሜትር ተረክቧል። በዚህ ቦታ ላይ ባንኩ የሚያሰራውን  የወደፊት የዋና መ/ቤት መንትያ ህንፃዎች በዘርፉ ከፍተኛ ልምድ ያላቸውን የህንጻ አርክቴክቸራል ዲዛይን ስራ ተቋራጮች ህጋዊ አካሄዱንና ስርአቱን በጠበቀ መልኩ እንዲሳተፉ በማድረግ በህንፃ ዲዛይን ስራ ግምገማ ሰፊ ልምድና  እውቀት  ያላቸውን ገለልተኛ የሆኑ   ዳኞች  እና  አማካሪዎችን  በማደራጀት  ለውድድር  ከቀረቡ  18  የህንፃ  ዲዛይኖች  ውስጥ  በገፅታው  እና  በይዘቱ   የባንካችንን አመሰራረትና  የወደፊት ጉዞ እንዲሁም የባንካችንን ማንነት የሚመስል ፤ በዘርፉ ባለሙያ በሆኑ ዳኞች  የተመረጠውን የህንፃ ዲዛይን በእስካይ ላይት ሆቴል በተደረገ ልዩ ስነ-ስርዓት የባንካችንን የወደፊት ዋና መ/ቤት ህንጻ ዲዛይን አሸናፊ መለየቱ የሚታወስ ነው ። በአሁን ሰአት ይህን የዋና መ/ቤት የህንፃ  ግንባታ ለማስጀመር የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎች ላይ እየተሰራ ይገኛል ።

ግሎባል ባንክ
ኢትዮጵያ
ለጋራ ስኬታችን


ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ
ዋና መስሪያ ቤት ፡- ኢትዮጵያ ሆቴል አካባቢ ናሽናል ታዎር
8118
www.globalbankethiopia.com
global Bank Ethiopia